# ኮሾ ተቃዋሚ!

*ሀማ ቱማ*



ድንጋይ ዳቦ ዘመን፣ ቃል ሚዛን ሲኖረው፣
መሃላ ቃል ኪዳን፣ ህሊናን ሲቃኘው፣
ይሁዳነት ርኩስ፣ ጴጥሮስነት ውርደት፣
ተብሎ ተወግዞ፣
ለእምነት መሰየፍን፣ ሰውን እየገራው፣
ህሊና ያን ክፉ ከርስ፣ ሁሌም እየገዛው፣
ሞት አይፈሬ ትውልድ፣ ደረቱን ለጥይት፣
ገላውን ለስየል፣ ለስቃይ፣
ቆርጦ እየለገሰ፣
ፀንቶ እያቃረበ፣
የሽብር ሰለባ፣
መከራ ሰቆቃ፣
አንድ መላ ትውልድ፣ ለሀገር ሲደማ፣
ጆሮ ዳባ ልበስ፣ ዓይናችን ይከደን፣
እኛ ምን አገባን፣ ቢጠበስ ቢሰቃይ፣
መላው ወገናችን፣
ብለው ተደብቀው፣
ለፋሺስት ያደሩ፣
ስደት የመረጡ፣
ዝምታንም አቅፈው፣ ህሊና የገደሉ፣
ነፍስ አልባ ፍጡሮች፣ ሀገር ያሳፈሩ፣
አለና ቢሉንም፣ ቆመው እየሞቱ፣
ደማቸው ተሟጦ፣ ሳይቆስሉ የሚደሙ፣
እጅ ወደላይ ስቅለው፣ ለፍርሀት ያደሩ፣
ትላንትም ነበሩ፣ ዛሬም ከእኛው አሉ።

ዘመን ተለውጦ፣ ማፈርም ተቀብሮ፣
መደበቁ ቀርቶ፣ መደንፋቱ ገኖ፣
እዩኝ እዩኝ ሰፍኖ፣
ለፈረንጁ ኩርኩም፣ ለጨቋኙ መንጋ፣ ጎንበስ ማለት መርጦ፣
ተቃዋሚ ነኝ ባይ፣ ጮሌው ተበራክቶ፣
አስመሳይ ማንዴላ፣ ተቃዋሚ ኮሾ፣
መጎንበሱ በዝቶ፣ መዋረድ በርክቶ፣
ቆሞ መታገሉ፣
ቃል ኪዳን ማክበሩ፣
በዓላማ መፅናቱ፣
ለሀገር መሞቱ፣
ለሕዝብ መሰዋቱ፣
ጭራሹን ተረስቶ፣
ኮሾው ተቃዋሚ፣ ታጋዩን ተክቶ።